## አዋጅ ቁጥር...../2011

## <u>የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ</u>

መድኃኒቶች ለጤና አገልግሎት አቅርቦት ወሳኝ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ እና ለዘርፉ የሚመደበው ከፍተኛ የሆነ መዋዕለ ነዋይ ዘመናዊ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሠራር መመራት ያለበት በመሆኑ፤

የመድኃኒት አቅርቦትን ለማሻሻል እና ሀገሪቱን ጥሩ ልምድ ያላቸው ሌሎች ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ ለማድረስ የዘርፉን የፋይናንስ ምንጭ፣ የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የአቅርቦት ሠንሠለት አመራር፣ የመሠረታዊ መድኃኒቶች መጠባበቂያ ክምችት መፍጠር እንዲሁም ተያያዥ አሠራሮችን በዘመናዊ ሁኔታ ለማጠናከር የሚያስችል በቂ የሕግ መሠረት በማስፈለጉ፤

በቂ፣ ቀጣይነት ያለው እና የህብረተሰቡን የመክፈል አቅም ያገናዘበ መድኃኒቶችን ትርፍን ባላማከለ ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያቀርብና ራሱን የሚደጉም ተቋም በዘመናዊ መልክ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1) **አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ “የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ...../ 2011” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) “መድኃኒት” ማለት የሰውን በሽታ፣ የተዛባ ወይም ጤነኛ ያልሆነ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ሁኔታ ወይም ተያያዥ ምልክቶችን ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚውል ማንኛውም ንጥረ-ነገር ወይም የንጥረ-ነገሮች ውህድ ሆኖ ባዮሎጂካል መድኃኒት፣ የህክምና መሣሪያ፣ ማሟያ ምግብ፣ የጤና ቴክኖሎጂ እና የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልግ ሌላ ማንኛውም ምርትን ያጠቃልላል፤

2) “መሠረታዊ መድኃኒት” ማለት በህግ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል ባወጣው የመሠረታዊ የመድኃኒቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ማንኛውም መድኃኒት ነው፤

3) “የህክምና መሣሪያ” ማለት የሚፈለገውን ተግባር ፋርማኮሎጂካል፣ ኢሚውኖሎጂካል ወይም ሜታቦሊክ ዘዴ በመጠቀም በቀጥታ የማያከናውን ማንኛውንም መገልገያ፣ ቅንብረ-መሣሪያ፣ መተግበሪያ፣ ማሽን፣ አፕሊያንስ፣ ሰውነት ውስጥ የሚቀመጥ ነገር፣ ናሙናን ከሰውነት ውጪ ለመመርመር የሚረዳ ውህድ ወይም የልኬት ማረጋገጫ፣ ሶፍትዌር፣ ዕቃ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁስ ሆኖ በአምራቹ ድርጅት ለብቻው ወይም በመቀላቀል ለሰው ህክምና ጥቅም ላይ እንዲውል የተዘጋጀ መሣሪያ ሲሆን ተያያዥ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ወይም እርግዝናን ለመከላከል የሚረዳ መሣሪያን ያጠቃልላል፤

4) “ማሟያ ምግብ” ማለት ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብ የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም የሰውነትን ተፈጥሯዊ አሠራር ላይ ውጤት ያላቸው የቫይታሚን፣ ማእድን ወይም ሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበትና በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ ካፕሱል፣ በእንክብል፣ ዱቄት፣ ፈሳሽ፣ ጠብታ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

5) “የጤና አገልግሎት” ማለት በህግ በተፈቀደለት የጤና ተቋም እና የጤና ባለሙያ የሥራ ወሰን መሠረት የሚሰጥ የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከም እና መልሶ የማቋቋም አገልግሎት እንዲሁም የጤና ምርመራ ላቦራቶሪ እና የህክምና ምርት ንግድ ሥራ ወይም አገልግሎት ነው፤

6) “የጤና ተቋም” ማለት የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን፣ የጤና ምርመራ ላቦራቶሪ ሥራን እና የህክምና ምርት ንግድ ሥራ ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፤

7) “መልሶ ማሸግ” ማለት የምርት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተጠናቀቀን እና በብዛት የተመረተን መድኃኒት መልሶ የማሸግ ተግባር ነው፤

8) “የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት” ማለት በጤና ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በተቀመጡት መመዘኛዎች መሠረት የተመረጠ የመንግስት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ መድኃኒት ቤት ነው፤

9) “የአደራ ግዥና ሽያጭ” ማለት በአደራ የተሰጠ ወይም የመጣ መድኃኒት ሲሆን ለዚሁ ቅብብሎሽ እንዲያገለግል በተዘጋጀ ቅጽ መዝግቦ በማስረከብ ወይም በመረከብ ተቀባዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለተሸጠው መድኃኒት ያህል ብቻ የመግዣ ዋጋው የሚከፍል ሲሆን ሳይሸጥ የቀረ መድኃኒት ቢኖር ግን ለአደራ ሰጪው ተመላሽ የሚሆንበት አሠራር ነው፤

10) “የማዕቀፍ ግዥ” ማለት ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽመው ኤጀንሲን በአንድ የጨረታ ሂደት ተወዳድሮ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠ አቅራቢን በግዥና የንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት በማዕቀፍ ግዥ መድኃኒት እንዲያቀርብ የሚያደርግበት የግዥ ሥርዓት ነው፤

11) “የተዋሀደ ግዥ” ማለት ፍላጎትን በማቀናጀት የተሻለ የዋጋ ጠቀሜታና ቀጣይነት ያለው አቅርቦትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ተቋማት ወይም አገራት የግዥ ፍላጎታቸውን በአንድ ላይ በማቀናጀት ግዥ የሚፈጽሙበት አሠራር ነው፤

12) “ስትራቴጇዊ የመጠባበቂያ ክምችት” ማለት ኤጀንሲው የሚያዘጋጀው እና ወቅታዊ ማሻሻያ የሚያደረግበት የተለዩ የመድኃኒት ዝርዝርን መሠረት ያደረገ ቢያንስ ለስድስት ወራት አቅርቦት የሚበቃ ክምችት ነው፤

13) “አቅራቢ” ማለት መድኃኒት ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር በማስመጣት ለኤጀንሲው ለማቅረብ ውል የገባ ማንኛውም ሰው ነው፤

14) “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

15) “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

16) “አግባብ ያለው አካል” ማለት በዚህ አዋጅ ላይ የተጠቀሱ ተግባራት በሚከናወኑበት ጊዜ ድርሻ ያለውና በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

17) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመድኃኒት ፈንድ

3) ***መቋቋም***

የመድኃኒት ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

4) **የፋይናንስ ምንጮች**

ፈንዱ የሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች ይኖሩታል፡-

1) በዘህ አዋጅ መሠረት ከመድኃኒት አቅርቦት ከሚገኝ የተጣራ ገቢ፤
2) ከመንግሥት በዓይነት ወይም በገንዘብ ከሚሰጥ ድጋፍ፤
3) ከለጋሽ አካላት በዓይነት ወይም በገንዘብ ከሚሰጥ እርዳታ፤እና
4) በዚህ አዋጅ መሠረት ከተፈቀዱ ሌሎች የገቢ ምንጮች እና ከተለያዩ ህጋዊ ገቢዎች፡፡

5) **የፈንዱ አጠቃቀም**

1) ፈንዱ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን እንዲሸፍን ከተደረገ በኋላ ተመልሶ በማዟዟር ለመድኃኒት ግዥ እና ለመድኃኒት አገልግሎት ማስፋፊያና ማጠናከሪያ እንዲውል ይደረጋል፡፡

2) የመድኃኒት አቅርቦት ቀጣይነት ለማረጋገጥ የፈንዱ ገንዘብ ለካፒታል ወጭ የሚውለው ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (3) መሠረት ሲወስን ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባራት

6) ***መቋቋም***

1) የኢትዮጵያ የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲው" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

2) ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

7) ***ዋና መሥሪያ ቤት***

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ፤ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

8) **ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) የመንግስት ጤና ተቋማት እና የማህበረሰብ ፋርማሲዎች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸው እና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶች በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ቀጣይነት ባለው እና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲያቀርቡ ማስቻል፤

2) የመድኃኒት አቅርቦትን በማጠናከር የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋትና ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ የመንግሥት የልማት ሥራዎችን መደገፍ፤

3) ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ የሆነ አሠራርን በመፍጠር መድኃኒቶችን ከብክነት እና ምዝበራ የሚከላከል የአቅርቦት ሥርዓት ማስፈን፤

4) የአቅርቦት ፍትኃዊነት እና የተገልጋይ እርካታን ያማከለ እንዲሁም የፋይናንስ እና ግዥ አስተዳደርን የሚመለከቱትን ጨምሮ ተፈጻሚነት ባለው የመንግሥት ሕጎች መሠረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያሰፈነ የአቅርቦት ሥርዓት መፍጠር፤ እና

5) ፈንዱን እና በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ሌላ ህግ መሰረት የተፈቀዱ የገቢ ምንጮች በመጠቀም ከላይ በዚህ አንቀጽ ስር የተጠቀሱቱን ዓላማዎች እውን ማድረግ ነው፡፡

9) **ስልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1) መሠረታዊ መድኃኒቶች እንዲሁም ስትራቴጂያዊ የመጠባበቂያ ክምችት ውስጥ የተካተቱ መድኃኒቶች ለመንግሥታዊ የጤና ተቋማት እና በጤና መድኅን ለታቀፉ የማህበረሰብ ፋርማሲዎች ለማቅረብ መልካም የግብይት አሠራር መርሆዎችን በተከተለ መልኩ ግዥ ያከናውናል፣ ያከማቻል፣ እስከ ጤና ጣቢያ ድረስ ያሰራጫል፤ እንደአግባቡ በበቂ መጠን ለገበያ ያልቀረቡ እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ ያልቀረቡ መድኃኒቶችን መንግሥታዊ ላልሆኑ እና ለግል ጤና ተቋማት ያቀርባል፤

2) ለቀልጣፋና ውጤታማ የመድኃኒት አቅርቦት አጋዥ የሆነ የግዥ፣ ክምችት እና ስርጭት ሥርዓት ያስፋፋል፣ ያጠናክራል፣ ይተገብራል፣ ይከታተላል፤ ዘመናዊ የክምችት አስተዳደር ሥርዓት ለማስፈን የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል፤

3) ዘመናዊ የመድኃኒት ማከማቻ፣ ማሸጊያ እና የስርጭት አውታሮችን ይዘረጋል፣ ያጠናክራል፤

4) በዘርፉ ከሚዘረጋው የስርጭት ሥርዓት ጋር የሚጣጣም ዘመናዊ የሎጅስቲክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ይዘረጋል፤

5) መድኃኒቶችን በቀጥታ ለጤና ተቋማት እንዲሁም በጤና መድኅን ለታቀፉ የማኅበረሰብ ፋርማሲዎች ለማድረስ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር ይዘረጋል፤ ይተገብራል፣ ይከታተላል፤

6) የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደርን ጨምሮ በሚያከናውናቸው የሥራ ዘርፎች ዙሪያ የሚሠራ የልህቀት ማዕከል ያደራጃል፤ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዳ የአቅርቦት ሠንሠለት የስልጠናና ምርምር ማዕከል ያቋቁማል፤ ዘርፉን የሚያሳድግ ምርምር ያካሂዳል፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

7) መረጃን መሠረት ያደረገ የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል እንዲሁም ለዓላማው መሳካት የሚረዳ የመረጃ ማዕከል ያደረጃል፤ የመረጃ መስፈርት፣ ምንጭ፣ መሰብሰቢያ መንገድ ይለያል፤ የተሰበሰበ መረጃ ተዓማኒ መሆኑን፣ ለውሳኔ የሚረዳ መረጃ በወቅቱ መሰብሰቡን እንዲሁም ማንኛውም የአቅርቦት ሠንሠለት ጋር የሚያያዝ ውሳኔ መረጃን መሠረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ከመድኃኒቶች አቅርቦት ጋር የሚያያዙ ለህዝብ እና ባለድርሻ አካላት መታወቅ ያለባቸውን ሁሉንም መረጃ ለህዝብ ይፋ እና በቀላሉ ተደራሽ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል፤

8) የሚያቀርባቸውን መድኃኒቶች የቁጥጥር መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚያግዝ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ያቋቁማል፤

9) አዋጭ ሆኖ ሲገኝ የተዋሀደ፣ የማእቀፍ ግዥ፣ የአደራ ግዥ እና ሽያጭ እንዲሁም የዱቤ ሽያጭ ያከናውናል፤

10) ፈንዱን ያስተዳድራል፤ ከመድኃኒቶች አቅርቦት አገልግሎት የሚገኘውን የገቢ ህዳግ ይወስናል፤

11) በየጊዜው የአቅርቦት ሠንሠለቱን ለመገምገም ለሥራ ማስኬጃ የወጣ ወጭን እና አፈጻጸሙን ይገመግማል፤ የእርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ማቆም ወይም መቀነስ አሉታዊ ተጽእኖ ለመከላከል

ያለውን የገንዘብ ምንጭ በሙሉ ከሥራ ማስኬጃ ወጭው አንጻር የሚያሳይ የፋይናንስ ቀጣይነት ግምገማ እቅድ ያዘጋጃል፤

12) አለምአቀፍ ድርጅቶችን ጨምሮ ከሌሎች አካላት ለሚኒስቴሩ በእርዳታ የሚሰጡ መድኃኒቶችን ተፈጻሚነት ያለውን የሚኒስቴሩን ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የአቅርቦት አስተዳዳደር ያከናውናል፤

13) ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ በግል ድርጅቶች ቢከናወኑ የተሻለ ቅልጥፍና እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙትን በጥናት በመለየት አገልግሎቱ በሌላ አቅራቢ  አካል እንዲሰጥ ስምምነት ይገባል፤ እንደአግባቡ ተፈጻሚነት ያለውን የመንግስት እና የግል አጋርነት የሚመራበትን ህግ መሠረት በማድረግ ከግል ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሠራል፤

14) ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር በተገናኘ ከሚሠሩ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ክልላዊ እና ከሌሎች ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

15) ፍትኃዊ የመድኃኒት  አቅርቦት እንዲኖር ሚኒስቴሩን፣ ክልሎችን እና ጤና ተቋማትን ጨምሮ በየደረጃው ካሉ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር የመድኃኒት እቅድ ዝግጅት ላይ በጋራ ይሠራል፤ በነዚህ አካላት ቢተገበሩ ዉጤታማ የሚያደርጉ ተግባራትን በመለየት ተቋማቱን ያግዛል፤

16) ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ መድኃኒቶች እና የህክምና ተረፈ-ምርቶች ማስወገጃ ኢንሲኒሬተር ይተከላል፣ ያስፋፋል፣ ያጠናክራል፣ ያስተዳድራል፤ በኢንሲኒሬተር ወይም በሌላ ተያያዥ መንገድ የማስወገድ አገልግሎት ይሰጣል፤

17) መድኃኒቶችን መልሶ በማሸግ እና ኪት በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲሁም ከሀገር ውጭ ይልካል፤ የግዥ፣ ክምችት፣ ስርጭት እና የሽያጭ አገልግሎትን ጨምሮ ተያያዥ ቴክኒካል አገልግሎት ይሰጣል፤ በዘርፉ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤ የተለዩ የህክምና መሣሪያዎችን ያከራያል፤ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ያቀርባል፤ ከመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ

ድርጅቶች ጋር አገልግሎት ለመስጠት የውል ስምምነት ይገባል፤ እንደአስፈላጊነቱ እህት ተቋማት ይኖሩታል፤

18) ኤጀንሲው ለሚሰጠው ትርፍን ያላማከለ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

19) የራሱ የባንክ አካውንት ይኖረዋል፣ ከአበዳሪ ተቋማት ገንዘብ ይበደራል፣ የንብረት ባለቤት እና የይዞታ ባለመብት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤ እንዲሁም

20) በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ወይም ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

10) **አደረጃጀት**

ኤጀንሲው፤

1) የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራ)፤
2) በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክትር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና
3) አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

11) **የቦርድ አባላት**

1) ቦርዱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየም ሰብሳቢ እና አግባብ ካላቸው የመንግስት ኃላፊዎች እንዲሁም እንደአግባቡ በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

2) የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል ይሆናል፡፡

3) ማንኛውም የቦርድ አባል በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋር የጥቅም ግጭት ማስወገድ ያለበት ሆኖ ከስራው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ማንኛውንም ተግባር ማከናወን

የለበትም፡፡ በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ጉዳይ ካለው ወይም የጥቅም ግጭት ሲያጋጥመው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች ሁሉ ራሱን ማግለል አለበት፡፡

4) የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ማንኛውም አባል ለተጫማሪ ሥራ ዘመናት እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡፡

5) ማንኛውም የቦርድ አባል በተደጋጋሚ የቦርድ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ያልቻለ እንደሆነ ቦርዱ ጉዳዩን ለሚኒስትሩ ማሳወቅ ያለበት ሆኖ ሚኒስትሩም ችግሩን ለመፍታት ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ በቸልተኝነት በተደጋጋሚ የቀረ፣ በፈቃዱ ከአባልነት የለቀቀ ወይም በሌላ ምክንያት መገኘት ያልቻለን አባል በቀጣይ የቦርድ ስብሰባ ላይ በሌላ አባል እንዲተካ በፍጥነት ያሳውቃል፡፡

6) የቦርዱ አባላት ጥቅማጥቅም የመንግሥት የፋይናንስ ሕግን መሠረት አድርጎ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

7) የቦርዱ ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

12) **የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ፡-

1) ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
2) የኤጀንሲውን የረጅምና አጭር ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅዶችን መርምሮ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

3) የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ መርሐ-ግብር፣ ዝርዝር በጀት እንዲሁም የካፒታል ወጪ እቅድ መርምሮ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

4) ኤጀንሲው የሚያስከፍለውን ትርፍን ያላማከለ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ይወስናል፤ የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5) የኤጀንሲው የፋይናንስ ፍላጎት እና ጥቅም ባስከበረ መልኩ ኤጀንሲው ከሀገር ውስጥ ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ መሠረት ባደረገ ሁኔታ የብድር አቅርቦት እንዲያገኝ ይወስናል፤

6) ኤጀንሲው የተከማቸ ሀብት ሲኖረው ጥናትን መሠረት በማድረግ የተወሰነውን ገንዘብ የግምጃ ቤት ሰነድ እና የመንግሥት የእዳ ሰነዶችን ጨምሮ በሌላ በተፈቀደ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ እንዲውል ይወስናል፤

7) መሠረታዊ የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ እና በቂ እና ብቃት ያለው ሠራተኛ ቅጥር፣ የአፈጻጸም ግምገማ፣ የተለየ የደመወዝና የማትጊያ ጥቅማጥቅም፣ አቅም ግንባታ፣ ምቹ የሥራ አከባቢ፣ ሠራተኛን ይዞ የማቆየት ሁኔታ እንዲሁም ሠራተኛን የማሰናበት ሥልጣንን ያካተተ የሠራተኞች አስተዳደር ዝርዝር መመሪያ መርምሮ ያጸድቃል፤

8) ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክትር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተርነት የሚቀርቡ ኃላፊዎችን ከሚኒስትሩ ጋር በመሆን በመንግሥት እንዲሾሙ ያቀርባል፤ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ያፀድቃል፤

9) አጠቃላይ የመንግስት ግዥ መርሆዎችን እና ይህንን አዋጅ መሠረት ያደረገ በኤጀንሲው የተዘጋጀ የግዥ መመሪያ መርምሮ ያጸድቃል፤

10) ከኤጀንሲው ቁልፍ ተግባራት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በግል ድርጅቶች እንዲከናወኑ የተለዩ ጉዳዮችን መርምሮ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

11) አጠቃላይ የመንግሥት የንብረት አስተዳደር እና ከመዝገብ የሚፋቁ ሒሣብ አሠራር መርሆዎችን መሠረት ያደረገ በኤጀንሲው የተዘጋጀ መመሪያ መርምሮ ያጸድቃል፤

12) ዓመታዊ የሒሣብ ሪፖርት ያጸድቃል፤ የኤጀንሲውን የፋይናንስ እና ሀብት አጠቃቀም የሚመረምር የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይሰይማል፤ የውስጥና የውጭ የኦዲት ሪፖርቶችን ያዳምጣል፤ በሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ ሪፖርቱንም ይፋ ያደርጋል፤

13) ኤጀንሲው ቅርንጫፍ እንዲኖረው ወይም እንዲዘጋ ይወስናል፤

14) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱ የራሱን ተግባራት በብቃት ለማከናወን ተለይተው የሚሰጡ የቦርዱን ተግባራት የሚያከናውን የቴክኒክ ኮሚቴ ይሰይማል፡፡

13) **የቦርዱ ስብሰባዎች**

1) ቦርዱ በሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን የቦርዱ ሰብሳቢ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ይጠራል፡፡

2) የቦርዱ የስብሰባ አጀንዳ ከስብሰባው ቀን ቢያንስ ከሦስት ቀናት በፊት ለቦርዱ አባላት መላክ ይኖርበታል፡፡

3) በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብላጫ አባላት ከተገኙ ምዕላተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

4) የቦርድ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

5) ማንኛውም የቦርዱ ስብሰባ በቃለ ጉባኤ የሚያዝ ሆኖ በስብሰባው ላይ በተሳተፉ የቦርድ አባላት መፈረም አለበት፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14) የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ኃላፊነት

1) የቦርዱ አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን የሥራ አመራር፣ ቴክኒካዊ እና የፋይናንስ ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ላይ ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በቦርድ የሚፀድቀውን የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ በመከተል የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ የዕቅድ አፈጻፀሙንም ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤

መ/ የኤጀንሲው ሒሣብ በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፤ የባንክ ሒሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ መሠረታዊ የሲቪል ሰርቪስ ህግ መርሆዎችን የተከተለ ዝርዝር የሠራተኛ አስተዳደር መመሪያ በማዘጋጀት ለቦርድ አቅርቦ ያስፀድቃል፤

ሰ/ በኤጀንሲው የሚሰጡ ትርፍን ያላማከለ የአገልግሎቶች የክፍያ ተመን መመሪያ አዘጋጅቶ በቦርድ ያፀድቃል፤

ሸ/ እንደ አስፈላጊነቱ የኤጀንሲውን ተግባራት በብቃት ለማከናወን የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

ቀ/ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

3) ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ኃላፊነቱ በከፊል ለኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ወይም በየደረጃው ላሉ ሌሎች ኃላፊዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

15) **የምክትል ዋና ዳይሬክቶሮች ስልጣንና ኃላፊነት**

1) ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

ሀ/ የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

ለ/ ተለይተው የሚሰጣቸውን የስራ ዘርፎች ያከናውናሉ፤ እንዲሁም

ሐ/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ዉክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

16) **በጀትና የኃላፊነት መጠን**

1) የኤጀንሲው በጀት በዚህ አዋጅ ላይ ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች እንዲሁም እንደአግባቡ በብድር ከሚገኝ ገንዘብ የሚሸፈን ሆኖ በቦርዱ መጽደቅ አለበት፡፡

2) የኤጀንሲው በጀት ዓመት የፌደራል መንግስቱ የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

3) ኤጀንሲው ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

17) **የባንክ ሒሣብ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተጠቀሰው ገንዘብ በኤጀንሲው ስም በዋናው መሥሪያ ቤት ወይም በቅርንጫፎች በተከፈተ የባንክ ሒሣብ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

18) **ስለ ክፍያ**

የኤጀንሲው ማንኛውም ገንዘብ ወጭ ሆኖ የሚከፈለው ለኤጀንሲው በጸደቀው ዓመታዊ የስራ ፕሮግራም ወይም በቦርዱ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

19) **ስለ ሒሣብ መዛግብት**

ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የተጠቃለለ የሒሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

20) **ኦዲት**

የኤጀንሲው የሒሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶችን በየዓመቱ በውጭ ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡ በኦዲተር የተመረመሩ የሒሣብ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ባለቀ ከአራት እስከ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባሉ፡፡

21) **መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር 553/1999 መሠረት የተቋቋመው የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኤጀንሲን ተላልፏል፡፡

22) **የጉምሩክ ቀረጥ እና ግብር**

የፈንዱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መድኃኒቶች ከጉምሩክ ቀረጥ፣ ግብር እና ተያያዥ የሆኑ የመንግሥት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድጋጌዎች**

23) **የመድኃኒት ግዥና አገልግሎት የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት**

1) አጠቃላይ የመንግሥት የግዥ ሕግ መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኤጀንሲው የመድኃኒትን ልዩ ባህሪ ታሳቢ ያደረገ የግዥ መመሪያ ይኖረዋል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ቢኖርም ጠባብ የፈዋሽነት ጠቋሚ ያላቸውን መድኃኒቶች፣ ልውጥ-ህያዉ ሥነ-ህይወታዊ ፋርማሲውቲካልስ፣ በሚያስከትሉት አደጋ ምክንያት ከፍተኛ የፈዋሽነት ጥንቃቄ የሚሹ መድኃኒቶች እና ክትባቶች ምርቶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፈጠረው አምራች፣ በዓለም የጤና ድርጅት እውቅና ከተሰጠው አቅራቢ ግዥ ሊያከናውን ይችላል፡፡ የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

ተፈጻሚነት ያለውን ህግ መሠረት በማድረግ ኤጀንሲው በግዥ ወቅት ሀገር ውስጥ ለሚመረቱ መድኃኒቶች ቅድሚያ በመስጠት የአገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታታበትን አሠራር ይፈጥራል፡፡ የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡ ማንኛውም የመንግሥት ጤና ተቋም የመሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጎታቸውን የኤጀንሲውን የመድኃኒት ግዥ መዘርዝር

መሠረት በማድረግ ለኤጀንሲው ብቻ በቀጥታ በማቅረብ ይገዛሉ፡፡ ኤጀንሲው የተጠቀሱትን ምርቶች ማቅረብ በማይችልበት ወቅት የአቅርቦት ፍላጎት ጥያቄውን መሠረት በማድረግ ተገቢውን መረጃ ይሰጣል፡፡

የመድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት የተሰጣቸው የጤና ተቋማት እና ሌሎች አካላት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ማስፈጸሚያ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት ለኤጀንሲው ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ይፈጽማሉ፡፡

5) ኤጀንሲው ክፍያ በወቅቱ ለማይፈጽሙ የጤና ተቋማት የመሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ጥያቄን ላይቀበል ይችላል፡፡ የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

24) **የቀጥታ ግዥ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ቢኖርም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ከሚኒስቴሩ ጋር በመስማማት መድኃኒቶችን ቀጥታ ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ አቅራቢ ቦርዱ በሚያወጣው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት በሚከተሉት ሁኔታዎች በቀጥታ ሊገዛ ይችላል፡-

1) ለህይወት አድን ተግባር አስፈላጊ የሆነ መድኃኒት ሲያልቅ እና ምርቱን በሀገር ውስጥ ማግኘት እንደማይቻል ሲረጋገጥ፤
2) የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ወይም ሌላ አደጋ ጊዜ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ የመድኃኒት እጥረት ሲከሰት፤ እንዲሁም
3) የመንግስት የግዥ ሕግን መሠረት አድርጎ በቦርድ በሚወሰን መመሪያ መሠረት ግልጽ ወይም ውስን ጨረታ ማድረግ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማይኖረው አነስተኛ ዋጋ ወይም መጠን ያለው ግዥ ሲሆን፡፡

25) **ስለመድኃኒቶች አወጋገድ**

ኤጀንሲው የመድኃኒት እና ሌላ ምርት ማሰወገድ ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት የሰው፣ የእንስሳ፣ እና የአከባቢ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ እና ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

26) **ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2) ኤጀንሲው ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ለሚወጣ ደንብ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

27) **ስለተሻሩ ህጎች**

የመድኃኒት ፈንድን እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 553/1999 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

28) **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**